NHS

# ለ NHS መረጃዎችዎ ትልቅ ትርጉም አላቸው (Your Data Matters)

የእርስዎን ጤና እና እንክብካቤ የተመለከቱ መረጃዎች የእርስዎን እንክብካቤ ለማሻሻል፣ ምርመራን ለማፋጠን፣ የአካባቢ አገልግሎቶችዎን ለማቀድ እና የአዳዲስ ሕክምናዎች ምርምርን ለማካሄድ ያግዙናል።

ግንቦት 2018፣ ይህ መረጃ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል እና እንደማይውል የሚገልጹት ጥብቅ ደንቦች ተጠናክረዋል። NHS የታካሚ መረጃ በጥንቃቄ ለማቆየት እና እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል ሁልጊዜ ግልጽ ለማድረግ ቁርጠኛ ነው።

---

ሚስጥራዊ የታካሚ መረጃዎ ለምርምር እና እቅድ ስራዎች ጥቅም ላይ ይውል እንደሆነ መምረጥ ይችላሉ።

ተጨማሪ ለማወቅ፡ የ **nhs.uk/your-nhs-data-matters** ድረ ገጽን ይጎብኙ።

---

ico. Information Commissioner's Office

YOUR DATA MATTERS

ስለ መረጃ መብቶችዎ የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎ መረጃዎችዎ ትልቅ ትርጉም አላቸው (Your Data Matters) ዘመቻን በ ico.org.uk ድረ ገጽ ላይ ይጎብኙ

## ሚስጥራዊ የታካሚ መረጃዎ ለምርምር እና እቅድ ስራዎች ጥቅም ላይ ይውል እንደሆነ መምረጥ ይችላሉ።

### መረጃዎ እንዴት ጥቅም ላይ ይውላል

የጤና እና የእንክብካቤ መረጃዎችዎ የእርስዎን የግል ክብካቤ ለማሻሻል ጥቅም ላይ ይውላሉ። በተጨማሪም አዳዲስ የሕክምና ዘዴዎች ላይ ጥናት ለማካሄድ፣ የ GP ክሊኒኮችን የት ቦታ እንደምናስቀምጥ ለመወሰን እና በአካባቢያዊ ሆስፒታልዎ ውስጥ የሚመደቡ ዶክተሮች እና ነርሶች ቁጥር ላይ እቅድ ለማውጣት እንዲረዳን ጥቅም ላይ ይውላሉ። በማንኛውም ቦታ የእርስዎን መረጃ የእርስዎ መሆኑን በማይታወቅበት ኣገባብ ለመጠቀም ኢንሞክራለን፤ ነገር ግን ኣንዳንድ ጊዜ ምስጥራዊ የታካሚ መረጃን መጠቀም አስፈላጊ ነው።

### ሚስጥራዊ የታካሚ መረጃ ምንድነው?

ሚስጥራዊ የታካሚ መረጃ እርስዎን የሚለይ እና ስለእርስዎ ጤና፣ እንክብካቤ ወይም ሕክምና የሆነ ነገር የሚገልጽ ነው። ይህ መረጃ ግላዊ ሆኖ እንዲያዝ ይጠብቁ ይሆናል። እንደ እርስዎ ስም እና አድራሻ ያሉ እርስዎን ብቻ ለይቶ የማያሳውቁ መረጃዎች እንደ ሚስጥራዊ የታካሚ መረጃ አይቆጠሩም እናም ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡- ለምሳሌ፣ የ GP ሕክምና ማዕከልዎ ከሌላ ጋር የሚዋሃድ ከሆነ እርስዎን ለማነጋገር።

### ለምርምር እና እቅድ ለማውጣት ሚስጥራዊ የታካሚ መረጃዎች ማን ሊጠቀም ይችላል?

በ NHS፣ በአካባቢ ባለስልጣናት፣ በዩኒቨርሲቲ እና በሆስፒታል ተመራማሪዎች፣ በሕክምና ኮሌጆች እና አዳዲስ የሕክምና ዘዴዎች ላይ ምርምር በሚያደርጉ የመድኃኒት አምራች ኩባንያዎች ጥቅም ላይ ይውላል።

### የመረጃዎን መርጦ-መውጣት ምርጫ ማድረግ

ለምርምርና እቅድ ማውጣት ሚስጥራዊ የታካሚ መረጃዎን ከማጋራት መርጠው መውጣትን መምረጥ ይችላሉ። በዚህ ሁኔታም ቢሆን፣ ሚስጥራዊ የታካሚ መረጃዎ ጥቅም ላይ የሚውልባቸው ጊዜዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡- ለምሳሌ፣ በእርስዎ ወይም በሌሎች ሰዎች ጤንነት ላይ አደጋ ሊደርስ የሚችልበት ወረርሽኝ በሚከሰትበት ወቅት። በዚህ ሁኔታም ቢሆን፣ በተወሰነ የምርምር ፕሮጀክት ላይ ለመሳተፍ መፍቀድ ይችላሉ።

### ይህን መርጦ-መውጣት መምረጥ በእርስዎ እንክብካቤ እና ሕክምና ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል?

አይኖረውም፣ በዚህ ሁኔታም፣ ሚስጥራዊ የታካሚ መረጃዎ ለግል እንክብካቤዎ ያገለግላል። መርጦ መውጣትን መምረጥ በእርስዎ እንክብካቤ እና ሕክምና ላይ ተጽዕኖ አይኖረውም። አሁንም ቢሆን እንደ አንጀት ካንሰር ላሉ የምርመራ አገልግሎቶች የሚጋበዙ ይሆናል።

### ቀጥሎ ምን ማድረግ አለብዎት?

ሚስጥራዊ የታካሚ መረጃዎ ጥቅም ላይ በሚውልበት መንገድ ደስተኛ ከሆኑ ምንም ነገር ማድረግ አያስፈልግዎትም።

ሚስጥራዊ የታካሚ መረጃዎ ለጥናት እና እቅድ ስራ እንዲውል የማይፈልጉ ከሆነ፣ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ በኢንተርኔት ወይም በስልክ አገልግሎት አማካኝነት መርጠው መውጣት ይችላሉ።

**ምርጫዎን በፈለጉ ጊዜ መቀየር ይችላሉ።**

የበለጠ ለማወቅ ወይም ምርጫዎን ለማድረግ የ **nhs.uk/your-nhs-data-matters** ድረ ገጽን ይጎብኙ ወይም በስልክ ቁጥር **0300 303 5678** ይደውሉ።

v1 5/18